## ከወያኔ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት የተገኘ ምስጢራዊ መረጃ

## ዲያስፖራውን ሀገር-ቤት ካለው ህዝብና የነጻነት ትግል የመነጠል ታላቅ ሴራ

**ተቀዳሚ አላማዎች :-**

አገርቤት ውስጥ ላለፉት 20 ዓመታት እየተካሄደ ያለውን ህዝባዊ ጸረ-ወያኔ ትግል በፋይናንስ፣ በቁሳቁስና፣ በዕውቀት፣ ወዘተ ያለማቋረጥ በማገዝና በመሳተፍ እዲሁም በጎንዮሽ ከሀገር ውጭ እየተደረገ ያለውን ዘርፈ ብዙ የዲፕሎማሲ ትግል ባለመሰልቸትና ባለመዘናጋት የወያኔ መሪዎችን በየደረሱበት የአለም ክፍል ሁሉ አየደረሰና እያሳደደ ሌት-ከቀን ፤ የአውሮፓና የሰሜን አሜሪካ አስቸጋሪ የአየር ጸባዮች ሳይበግረው ለሰላም፣ለፍትህ፣ለነጻነት፣ለዲሞክራሲና እኩልነት የሚያደርገውን ሁለገብ ትግል ከየአቅጣጫው በማቀጣጠል መቆሚያና መቀመጫ ያሳጣቸውን "ዲያስፖራ" አገርቤት ካለው ህዝብ ጋር መነጠልና እርስ በራሱ በማናከስ ለመበታተንና ለመከፋፈል ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ እየተደረጉ ካሉት ታላላቅ የወያኔ ሴራዎች አንዱና ዋነኛው ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ እንደሚከተለው ይነበባል።

ሁለት አመታት የሚያስቆመው አጥቶ እንዲሁ በሜዳ የምን-ግዴ ከበሮ ሲደለቅለት የከረመው የወያኔው ታሪካዊ የ3 ዓመታት ተከታታይ የ10% የኢኮኖሚ እድገት "እውነትና ንጋት እያደር ይጠራ" እንዲሉ ጊዜው ደረሰና የህልም-አለም ላይ የተንጠለጠለው የእድገቱ ባቡርና እርሱን ተከትሎ የተወለደው መነሻና መድረሻው የማይታወቀው፤ ምንነቱና ማንነቱ ቅጥ-አምባሩ የጠፋው የወያኔው "የ5 ዓመቱ የትራንስፎርሜሽንና የዕድገት" እቅድ ሳይጀመርና ስንዝር ሳይጓዝ እንዲሁ በሜዳ ተንገራግጮ ሊቆምና እውነቱ እርቃኑን ሊቀር እነሆ የመጨረሻው መጨረሻ ሰዓት ወይም ሰውያቸው እንዳለው "11ኛው ሰዓት" ላይ ይገኛል። ይባስ ብሎ አበው "ትለብሰው የሌላት የምትከናነበው አማራት" እንዲሉ በልመና እንኳን አልሞላ ካለው የሃገሪቱ አመታዊ ባጀት 70 ሚሊዮን ዳላር በ10 ሚሊዮን ብልጫ አለው የተባለውን የ "አባይን እገድባለሀ" የማደናገሪያ ድንፋታ በመጠቀም "ቡናን ኤክስፖርት በማድረግ ከምናገኘው የውጭ ምንዛሬ በላይ ከፍትኛ ገቢ አስገኝቶልናል" የሚሉትን እናት ላማቸውን/ዲያስፖራውን ዳግም ለማለብ እየተደረጉ ካሉት እኩይ ሴራዎች አንዱና ዋነኛው ነው።

**ትግበራ :-**

**1ኛ. በሁሉም የሰሜን አሜሪካ ግዛቶች በተመሳሳይ ቀንና ሰአት ስብሰባዎችን በማከናዎን "የዲያስፖራውን" አንድነትና ህብረት በሰው ሃይልና በመረጃ እጦት ማዳከም፤**

ይሄ አይነቱ አካሄድ ወያኔ ከዚህ ቀደም በሀገር ቤት በከፍተኛ ሁኔታ ይቃወሙኛል፤ እንዲሁም ለተልእኮዬ ከፍተኛ እንቅፋት ሆነውብኛል በማለት በጀምላ የሚከሳቸውን ለማጥቃትና ለመከፋፈል በተደጋጋሚ የተጠቀመበት ስልት ቀጥተኛ ግልባጭ ነው።

**ታሪካዊ ማስረጃ ቁ. 1**

በተለይም በዋናነት መላው የኢትዮጵያ መምህራን ለዚህ የወያኔ ጥቃት ግንባር ቀደም ኢላማ በመሆን ተጠቃሽ ናቸው። ዘወትር በወያኔ ለሚከሰሱበት ተቃውሚቸው/ጥፋታቸው እጅግ በከፋ የኑሮ ድህነትና ወከባ ውስጥ እንዲቆራመዱና ትውልድ ገዳይነቱ በተረጋገጠ የት/ርት ፖሊሲ አስገዳጅነት ዘወትር የሚሳሱለትን፣ ለእድገቱና ለነጻነቱ የሚታገሉለትን ወገናቸውን፣ የነገ ተሰፋቸውን በተለይ ወጣቱን ትውልድ በገዛ ጠመኔያቸውና ሙያቸው/ልሳናቸው መርዝነት እንዲገሉ

በወያኔ የአደንቁረህ ግዛ የት/ርት ፖሊሲ ውስጥ እንዲሰሩ የተበየነባቸው ጭቁን የኢትዮጵያ መምህራን ሀገራዊ ተቃውሟቸው አይሎ አላላውስ፤አላንቀሳቅስ ሲለው በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን መምህራን/ምሁራን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተመሳሳይ ወቅትና ጊዜ ወያኔ አሉኝ የሚላቸውን ካድሬዎቹን ለራሳቸው እንኳን ያልገባቸውንና በየትኛውም ወቅትና ሁኔታ ተገምግሞ የማያውቀውን የ5 ዓመት ዕቅድ-ወዝባዝንኬ በማስታቀፍና በማሰማራት በአንድ ጊዜና በተመሳሳይ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ በየአዳራሹ አጉሮ በየአመቱ ህምሌ በመጣ ቁጥር ሲያደነቁር መኖሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ( ለዋቢነት አቶ መለስ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንን እየሰበሰበ በየጊዜው ያሰማ የነበረውን ዲስኩር ማስታወስ በቂ ይመስለኛል)

እንግዲህ በዚህ አይነቱ የተለመደ ዘዴ የተቃኘው የሰሞኑ የህወሃት/ወያኔ ጸረ-አንድነትና ጸረ-ኢትዮጵያዊነት ሃይሎች የጥቃት ዘመቻ የሚከተሉትን ሁለት ዋና ዋና ግቦች ያነገበ ነው። ይኃውም :-

- በተለያየ ቦታ የሚገኘው የህ/ክፍል እንደተለመደው መረጃዎችን በመለዋወጥ እኩዩን የወያኔ ከፋፋይ ሴራ ተረድቶ እራሱን ፣ ሀገሩንና ህዝቡን ከዚህ ክፉ የጥፋት ወጥመድ እንዳይታደግ ለማድረግና ፤
- እንደሚታወቀው ሁሉ እዚህ በስደት የሚኖረው ወገናችን የወያኔ ቡችሎች በደረሱበት ሁሉ በአንድነትና በህብረት እየቆመ ከከተማ ከተማ እየተንከራተተ እያሳደደ እንደተለመደው የጥፋት አላማቸውን ሰላሚያኮላሽባቸው ይህን ህብረቱን፣ አንድነቱንና ሀይሉን ለማዳከም የታለመ ነው።

## 2ኛ. በምስልና ድምጽ /ቪዲዮ/ በተደገፈ መረጃ የሚፈጸም የማወናበድ ድራማ:-

በመላው አሜሪካ የሚደረገውን ስብሰባ በመቅረፅ በቀጥታ ስርጭት/live show/ ወደ ሀገር ቤት በተለመደው የወያኔ ቆርጦ የመቀጠል ዘዴ ምስሎቹን እየቆራረጡና እየቀጠሉ በማስተላለፍ ሀገር ቤት ለሚገኘው በረሃብና በችጋር ለሚገርፉት ህዝባችን በውጭ የሚኖረው፣ መመኪያ ወገኑ ጽኑ ወኔ በስመ ልማትና ኢንቨስትመንት መሰለቡንና ከነጻነት ትግሉ መነጠሉን፤ ብሎም በቻውን ያለአጋር እንደቀረ በማስመሰል እንደተለመደው እውነት በማያውቀው ቴሌቪዥናቸው ቋቅ እስኪለው ማሳየትና ዲያስፖራውም ወደ ሀገሩ ለመመላለስ ከወያኔ ደህንነቶችን ይልቅ ወገኑን እንዲፈረና እንዲሸማቀቅ ማድረግ ፤

ይህ አይነቱ አካሄድ ወያኔ ከስረ-መሰረቱ ሲጠቀምበት የኖረና በአብዛኛው ጊዜ ጥቂት ደካማዎችን ያወናበደበትና ውጤታማ አድርጎኛል ብሎ የሚኮፈስበት የከፋፍለህ ግዛ ስልቱ አብይ ዘዴ ነው።

## ታሪካዊ ማስረጃ ቁ. 2

በወያኔ አቅድ አውጭነትና አዝማችነት እንዲሁም በደርግ ባለስልጣናት ውሳኔና የጦር ጀቶች ጨፋጫፊነት በሀውዜን ህዝብ ላይ ከደረሰው ትውልድ ይቅር የማይለው የግፍ ጭፍጨፋና ወንጀል እስከ አምናው የእነ ጀነራል ተፈራ ማሞ የመፈንቅለ-መንግስት ድራማና እስከ ሰሞኑ የወ/ት ብርቱካን የዳግም ይቅርታ ቧልት የምንረዳው አብይ ቁምነገር ቢኖር ወያኔ በዚህ መንገድ ምንያህል እንደ ሰየጠነበት ብቻ ይሆናል። በመሆኑም:-

የአሁኑ በምስልና ድምጽ /ቪዲዮ/ በተደገፈ መረጃ በሚቀናበር ድራማ ሰለባ ሊሆኑ የተደገሰላቸው ፤ እስከዛሬ ድረስ በተለያዩ መንገዶች እንደ አይጥ በተቀመመላቸው ገዳይ መርዝና በተጠመደላቸው የጥፋት ወጥመዶች ሁሉ ግዳይ አልወድቅ ብለው ያስቸገሩት፤ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች የነጻነት ትግል የጀርባ አጥንቶች በመሆን ሌት ከቀን እንደተርብ የሚራወጡት፤ በመላው አለም ካሉት አምባገነንና ጭራቅ መሪዎች በተለየ ሁኔታ የወያኔን ዘረኛ መሪዎች በየታዩበት

መድረክ ሁሉ እያሳደደ በአለም አደባባይ እያዋረደ እንደ ሽኮኮ ወደጉድጓዳቸው በሰቀቀን የመለሳቸው፤ ከበርሃ ጀምረው እንደ ልባቸው የፋለሉበትንና በነጻነት ትግል ስም በሚሊዮን ዶላሮች ያፈሱበትን የዲፕሎማሲውን መድርክ አንቆ የያዘባቸውና ቀደም ሲል በተራቡት የትግራይ ህጻናትና እናቶች ስም የዘረፉትን በሚሊዮኖች የሚቆጠር የዶላር ሽርፍራፊ ሳይቀር እያጋለጠ በየመድረኩ እርቃናቸውን ያስቀራቸውና አጋሮቻቸውን ሳይቀር የሃፍረት ሸማ ያከናነበባቸው፤ በአጠቃላይ እንደ አማራ እና ኢትዮጵያዊነት ሁሉ ቀደም ባሉት ዘመናት ተፈፕሮላቸው ቢሆን አብረው ሊዘምቱበት ይገባ የነበረው ዋነኛው የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያዊነት አለኝታ የሆነውን ቀንደኛ ጠላታቸውን "ዲያስፖራው"ን ( ምን ያደርጋል የኢትዮጵያውያን የስደት ዘመን እድሜ የሚለካው/የሚቆጠረው ከወያኔ መፈጠር ማግስት ሆነና ለፕሮፖጋንዳና ለጥቃት አልመቻቸው አለ) እያደረሰባቸው ያለውን ፈርጀ ብዙ ጥቃትና መከራ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስቆም የተዘመተ- የጥፋት ከተት- ዘመቻ ፀረ-ዲያስፖራ

## 3ኛ. ከቀረጥ ነጻ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች እና ቁሳቁስ የማስገቢያ ፈቃድ፤ ዲያስፖራ የመደለያ ጉርሻ

ይህ መንገድ በመጠኑም ቢሆን ጥቂት የማይባሉ የዲያስፖራውን ጎራ አባላት እንደሚያማልል በወያኔ ዘንድ ግንዛቤ ተወስዷል። ምክንያቱም የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ክብሩና ኩራቱ፣ ጌጥና ማዕረጉ በሃገሩ መሬት መሆኑና ለሃገሩና ለወገኑ ያለውን ፍቅር ታሳቢ ያደረገ ነው። ዜመኛው "ማን እንደ እናት ማን እንድ ሃገር...." እንዳለው ማለት ነው። ሰለዚህ ይህን የጎን ውጋት በመሆን አላስቀምጥ አላስቀም ያለውን ጠንቀኛ ጠላት ለመበታተን ይቻል ዘንድ በሃገሩ ምድር ሊያሽከረክረው የሚጓጓለትን የዘመኑን ቴክኖሎጂ የተራቀቀበትን ቅንጡ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነጻ በማስገባት በራሱ ሀብት ገመድነት ለማነቅ የተዘጋጀ ታላቅ ሴራ ነው።

## ታሪካዊ ማስረጃ ቁ. 3

ከዚህ ቀደም እንደሚታወቀው የወያኔ የማፊያ ሀገር ዘራፊ ቡድን አባላት የሀገሪቱን የመኪና ሽያጭ ገበያ እንዳሻቸው እንዲፈነጩበትና በህገወጥ መንገድ ህዝቡን በመዝረፍ ያለ አግባብ እንዲበለጽጉ የተዘረጋ ህጋዊ የዝርፊያ መንገድ ነበር። በወቅቱ የተከፈተውን የዝርፊያ መንገድ በመጠቀም ሌሎች የማይፈለጉ ወይም በተለይ ወያኔ በቁጭት ዘወትር "የአዲስ አበባ ጩሉሌዎች" እያለ የሚያነሳቸው የህ/ሰብ ክፍሎች ባልተጠበቀ ሁኔታ ቢዝነሱን በመረዳታቸው ዝርፊያው ውስጥ በብዛትና በጥራት በመሳተፍ "የአባትህ ቤት ሲወረር አብረህ ውረር" እንደሚባለው በምዝበራው ወያኔዎች ባስደነገጠ ሁኔታ በልጠው በመገኘታቸው ለጊዜው መንገዱ በአስቸኳይ ትእዛዝ እንደተዘጋ የታወቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ በስመ ኢንቨስትመንትና ልማት በተለያዩ ጊዜያት ከቀረጥ-ነጻ የተለያዩ ቁሳቁሶች እንዲገቡ መፍቀዱ የታወቃል። በዚህም ዘዴ ከፉኛ ተታለው ወደሃገር ቤት የገቡ/ ንብረት ያስገቡ/ ጥቂት የዋህ ወገኖች ፈልገውም ይሁን ሳይፈልጉ በገቡበት በአቋራጭ የመበልጸግ ወያኔያዊ ወጥመድ ባለማስተዋል በመውደቃቸው በራሳቸው ሀብትና ንብረት የመሰቀያ ገመድነት ታንቀውና አኩሪ የጀግንነት ታሪካቸውን አጉድፈው ከነጻነት ትግሉ ጎራ በውርደትና በጸጸት መውጣታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

በአሁኑ ሰአት ሁሉም ከዲያስፖራነት ወደ ሀገር ቤት ተመልሶ የነበረው ወገናችን የቻለ የጀመረውን ቤትም ይሁን ድርጅት በመዝጋት እግሬንና ነብሴን አውጭኝ ወደመጣበት ሲፈረጥጥ፣ ያልቻለው ደግሞ በብስጭትና በእልህ ውድ ሂዎቱን ለማጠፋት ተገዷል። ቀሪው ወገናችን - ከሞቱት በላይ ካልሞቱት በታች በመሆን - በገዛ ንብረቱ ወንጀለኝነት ተከሶ

በየፍርድቤቱና በየማጎሪያ ጣቢያው በመንገላታት ላይ ይገኛል። ይህን አሳዛኝ እውነታ ሀገር ቤት በሚታተመውና በወያኔ አፍቃሪነቱ በሚታወቀው የተጋዳላይ አማረ አረጋዊ ሪፖርተር ጋዜጣ የዕረቡ ማርች 23 2011 እትም ላይ ክቡር ሚኒስትር በሚለው አምድ ስር "በሥራ ምክንያት ውጭ አገር በሔዱ ቁጥር ክቡር ሚኒስትሩ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን አገራቸው ገብተው በእውቀታቸውና በገንዘባቸው እንዲሠሩና የልማት አጋር እንዲሆኑ ይወተውታሉ" የሚለውን መጣጥፍ መመልከት ከበቂ በላይ ነው።

## 4ኛ. የቦንድ ሽያጭ ፋሽን

በከፈተኛ የውጭ ምንዛሬ እጦት ጣረሞት ላይ ያለውንና በእየለቱ ከላይ ከራሱ ጀምሮ እስከ እግር ጥፍሩ እርቃኑን እየቀረ የሚገኘውን የወያኔ አደንቋሪ እድገት ለመታደግና ለጊዜውም ቢሆን አይቀሬውን ከሰሜን አፍሪካ የተነሳውን ህዝባዊ ማዕበል አቅጣጫ ለማስቀየር ከየአቅጣጫው አሳሩን የሚያየው የወያኔ ቡድን በቅድሚያ በሃገር ቤት የራሱን አሻንጉሊቶቹን በተለይም ለጊዜው በዋናነት ኦህዴዶቹን የቃየል መስዋዕት በማድረግና ቤተ-እምነቶችን በማተራመስ የዘለቀው እስትንፋስ የማቆየት ዘመቻ በዲያስፖራው በኩል ደግሞ የአለም የደሃ ውራ የሆነች ሀገር አባይን በ80 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ለመገደብና ለማልማት አቅጃለሁ በማለት በተለመደ ወያኔያዊ ቅጥፈት በመጠቀም በወያኔ የግፍ አገዛዝ ተይዞ በረሃብና በችጋር ለሚቆራመደው ወገኑ የሚልከው ዶላር ያስጎመዠው ወያኔ የቋመጠለትን ዶላር ለማፈስ እዚሁ ቤታችን ድረስ በቦንድ ሽያጭ ዲስኩር ታጭቀው መጥተዋል። ስለዚህ፡-

## *ልብ ያለው ልብ ይበል*

ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸውና በተለያዩ ወቅታዊ ሁኔታዎች የግባዕተ-መሬቱ አይቀሬነት የተረጋገጠው በሙስና፣ሀገር በማፍረስ እና በህዝቦች የጅምላ ጭፍጨፋ ወንጀሎች አንገቱ ድረስ የተዘፈቀው የወያኔ ጭራቅ ቡድን የመጨረሻውን የሞት ትግል እያደረገ የሚገኝ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ለአለፉት ፳ት ዓስርት አመታት ሲጨቁኑት የነበሩትን አምባገነን ፊዎዳላዊውን የዘውድ አገዛዝና ጨካኙን የደርግ መንግስት በመራራው የህዝቦች ትግልና በውድ ልጆቹ ክቡር መስዋዕትነት አዋርዶና ዳግም እንዳያንሰራሩ አድርጎ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከላዩላይ አሽቀንጥሮ አንደጣላቸው ሁሉ በኢትዮጵያ ህዝብ መራራ የነጻነት ትግል ውስጥ የበግ ለምድ ለብሶ ስልጣን ላይ የወጣውን አረመኔውንና ከሃዲውን የወያኔ ቡድን እንደ መሰል አምባገነን ወንድሞቹ ዳግም በኢትዮጵያ መሬት እንዳይፈጠር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ግባዕተ-መሬቱን ለማረጋገጥ የሚደረገው መራራ ህዝባዊ ትግል የመጨረሻው መጨረሻ ሰዓት ላይ ይገኛል።

ስለዚህ በመላው ሰሜን አሜሪካ ግዛቶች ካናዳን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቅዳሜና እሁድ ማለትም ***April 9 & 10 2011*** በሚደረጉ የወያኔ ስብሰባዎች ባለመካፈልና በነዚሁ እለታት በሁሉም ከተሞች በሚደረጉ ህዝባዊ የተቃውሞ ሰልፎች በንቃትና በትጋት መሳተፍ ማለት ቆራጥ ማንነትና የትግል ጽናትን ማረጋገጫ፣ ታሪካዊ ሃላፊነትንና ሃገራዊ አደራን መወጫና በሃገር ቤት በሁሉም አቅጣጫ ለተፋፋመው ህዝባዊ ትግል የወገን አለኝታነታችንና ጭቁኑ ህዝባችን እያደረገ ላለው የነጻነት ትግል ታማኝ የዘለዓለም አጋርነታችን ማረጋገጫ የመጨረሻው መጨረሻ ቃልኪዳናችን መስጠት ማለት መሆኑን **ልብ** ልንል ይገባል። እንግዲህ ***ልብ ያለው ልብ ይበል !!***

***ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በክብር በነጻነትና በአንድነት ጸንታ ትኑር !!***

**ኪዴ- ዘጫቆ**